# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር

# የአጠቃላይ ትምህረት ዘርፍ ትምህርት ቤቶች የወላጅ፣ ተማሪ፣ መምህር ህብረት አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ

# ቁጥር 993/2016

# መመሪያ ቁጥር 993 /2016

## የትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ት/ቤቶች የወላጅ፣ ተማሪ፣ መምህር ህብረት አደረጃጀትና አፈጻፀም መመሪያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የዜጎችን ፍትሐዊ የትምህርት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ፖሊሲ ቀርጻ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ስታከናውን ቆይታለች፡፡ከነዚህም ስራዎች ውስጥ በውጭ ሀገር የሚኖሩ አትጵያዊያን የሚማሩበት የማህበረሰብ ት/ቤት ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የውጭ ሀገር ዜጎች የሚማሩበት የማህበረሰብ ት/ቤት፣ በውጭ ሀገር ባለሃብቶች የሚቋቋሙ ት/ቤቶችና ዓለም አቀፍ ት/ቤቶች እንዲቋቋሙ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ፍትሐዊ የትምህርት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተሰሩ ስራዎች ማሳያዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በነዚህ ት/ቤቶች ውስጥ የሚማሩ የተማሪ ወላጆችና ባለድርሻ አካላት ከት/ቤቱ ጋር ተቀራርበው በሚኖራቸው ተሳትፎ ተገቢ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር የበኩላቸውን እንዲወጡ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የወላጆች፣ተማሪዎች፣መምህራንና እና ባለድርሻ አካላት በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ መሳተፍ ጤናማና ፍትሐዊ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ጉልህ ድርሻ ያለው መሆኑ ስለታመነበትና ይህ ስራ የሚመራበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የተማሪ ወላጆች፣ተማሪዎች፣መምህራንና ባለድርሻ አካላት በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ በመሳተፍ የበኩላቸውን እንዲወጡ ለማስቻልና በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት ይቻል ዘንድ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 34 (ሀ) መሰረት የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ት/ቤቶች የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ አውጥቶአል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ት/ቤቶች የወላጅ፣ ተማሪ፣ መምህር ህብረት አደረጃጀትና አፈጻፀም መመሪያ ቀጥር 993/2016 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1/ "የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት" ማለት ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ት/ቤቶች፣የተማሪ ወላጆች፣መምህራንና ተማሪዎች ስብጥር ያለው አደረጃጀት ነው፡፡

2/ "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት በትምህርት ቤቱ የሚማሩ የተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች፥መምህራን እንዲሁም ተማሪዎች ከህብረቱ ውጪ ለብቻቸው የሚያደርጓቸውና የሚሳተፉበት ጠቅላላ ስብሰባ ነው፡፡

3/ "የማህበረሰብ ት/ቤት" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የውጭ ሀገር ዜጎች እና ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ልጆቻቸውን በሀገራቸው ስርዓተ ትምህርት ለማስተማር እንዲችሉ የሚቋቋም ትምህርቶች ቤት ነው፡፡

4/ "በውጭ ኢንቨስትመንት የተቋቋመ ት/ቤት" ማለት በከፊል ወይንም ሙሉ በሙሉ በውጭ ባለሃብት የተቋቋመ ት/ቤት ማለት ነው፡፡

5/ "ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች" ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ተቋቁመው ወይም ተመዝግበው በኢትዮጵያ ወይም በሌላ ሀገር ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት የትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው።

6/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ ሁኔታ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም የትምህርት ሚኒስትር ነው፡፡

7/ በዚህ መመሪያ በወንድ የተገለጸ የጾታ አገላለጽ ለሴቶችም ያገለግላል፡፡

### 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ በመመሪያ ከትምህርት ሚኒስቴር ፈቃድ ተሰጥቶአቸው የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ስር ስራ ላይ በተሰማሩ ት/ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. አላማ

የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ስራ ላይ የተሰማሩ ትምህርት ቤቶች ወላጅ ፥መምህርና ተማሪ ህብረት አደረጃጀትና ተሳትፎ ላይ ወጥ የሆነ የአሰራር ስርአት እንዲኖር ማስቻል ነው።

# ክፍል ሁለት

# የወላጅ፣ተማሪ መምህር ህብረት አደረጃጀት

## 5. የወላጅ፣ተማሪ መምህር ህብረት አባላት ብዛትና ስብጥር

1/ የት/ቤት ወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም ሲሆን ከ7 እስከ 9 አባላት የሚኖሩት ይሆናል፡፡

2/ ምርጫውም 3 አባላት ባሉት አስመራጭ ኮሚቴ ይከናወናል፡፡

3/ አባላቱም ለሁለት ጊዜ/ተርም/ ሊመረጡ ይችላሉ። ሆኖም ጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ሊለውጥ ይችላል።

4/ ምርጫ በሚከናወንበት ወቅት የትምህርት ሚኒስቴር ትምህርት ጥራት ዘርፍ ተወካዮች እንደአስፈላጊነቱ ባሉበት የሚከናወን ሆኖ ጠቅላላ ጉባኤው አባለት ወይም የተማሪ ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች መካከል 51 በመቶ በላይ በተገኙበት ይከናዎናል፡፡

5/ የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት አስመራጭ ኮሚቴ አባላት

ሀ) የት/ቤቱ የበላይ ተጠሪ/ የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር፣

ለ) በምርጫ ወቅት ከወላጅ የሚወከሉ 2 በአጠቃላይ 3 አባላት ይኖሩታል፡፡

## 6. የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት አባላት የመመልመያ መስፈርቶች

1/ በመልካም ስነ-ምግባር የተመሰገነ እና የማስተባበር ችሎታ ያለው፣

2/ በወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት በቁርጠኝነት ለማገልገል ፈቃደኛና ዝግጁ የሆነ፣በትምህርት ቤቱ የሚማር ልጅ ያለው፣ በትምህርት ቤቱ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚደገፍ ተማሪ ወይም ወላጅ ያልሆነ፣

3/ ሀይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ወገንተኝነትን የማያንፀባርቅ፣

4/ ያታዊ ምጥጥን ታሳቢ ያደረገ ምልመላን ይካሔዳል፣

## 7. <u>የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት አባላት</u>

1/ በወላጆች ጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ 2ሰብሳቢና ምክትል

2/ ከመምህራን ጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ 2 1 ፀሀፊና 1 አባል

3/ የወላጅ ተወካዮች 3 አባላት

4/ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 2 /ሁለት/ የተማሪ ተወካዮች በአባልነት የሚወከሉ ሲሆን በአፀደ ህፃናት እና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የተማሪ ተወካይ አይኖርም፡፡

5/ የተማሪ ተወካዮች የሚመረጡት በተማሪዎች ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል።

## 8. <u>የሕብረቱ የስብሰባ ጊዜ</u>

1/ የህብረቱ የስብሰባ ጊዜ በቋሚነት በወር አንድ ጊዜ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ የመሰብሰቢያ ግዜውን ሳይጠብቅ አሰቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

2/ ህብረቱ ስብሰባውን ለመካሄድ ከአባላቱ 51 በመቶ በላይ መገኘት አለበት፡፡ ሆኖም ግን የህብረቱ አባላት ሁለት ጊዜ ጥሪ ተደርጎላቸው ሰብሰባውን ለማካሄድ የሚየስፈለገው የሰው ሀይል ባይሟላ በተገኙት አባላት ሰብሰባውን የሚካሄድ ሲሆን ውሳኔአቸው በህብረቱ አባለት በሙሉ እንደተወሰነ ይቆጠራል፡፡

## 9. <u>ወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት (ወተመህ/ወመህ) ኃላፊነትና ተግባራት</u>

1/ ከተግባርና ኃላፊነታቸው ጋር የተያያዙ የሥራ ዕቅዶችን በማዘጋጀት በወላጆች ጠቅላላ ጉባዔ በማስወሰን ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቅርቦ ተግባራዊ ማድረግ፣

2/ የትምህርት ቤቱ ዓመታዊ ዕቅድና የማስፈጸሚያ ስልቶች እንዲሁም ሌሎች የውስጥ መመሪያዎች ሲነደፉ አስተያየት መስጠት፣

3/ በየሩብ ዓመቱ የታቀዱ የመማር ማስተማር ስራዎችን መገምገም፣

4/ በትምህርት ቤት በሚደረግ የትምህርት ክፍያ እና የክፍያ ጭማሪ ላይ ከትምህርት ቤቱ እና ተማሪ ወላጆች ጋር በመወያየት በትምህርት ሚኒስቴር ማህበረሰብ ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የትምህርት ቤቶች ፈቃድ አሰጣጥ እና እድሳት መመሪያ ቁጥር 992/2016 መመሪያ መሰረት ስምምነት ላይ መድረስ፣

5/ ለየትምህርት እርከኑ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ተገቢውን መምህራንና ሰራተኞች መሟላታቸውን መከታተል

6/ መምህራን የሚጠበቅባቸውን የማስተማር ተግባር በትክክል መፈጸማቸውን ማረጋገጥ፣

7/ ሙያዊ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የማይወጡትን መምህራን ደረጃውን ጠብቆ በመምከር ማስተካከል፣

8/ ሙያዊ ኃላፊነቱን በአግባቡ የማይወጣ ርዕሠ መምህር በመምከር ማስተካከል፣ በምክር የማይመለስ ከሆነ ጉዳዩን በትምህርት ቤቱ ባለው የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርአት መሰረት ለሚመለከተው ክፍል በማቅረብ ውሳኔ እንዲያገኝ ተገቢውን ስራ መስራት፤

9/ በትምህርት ቤት ደረጃ ሊወስኑ የሚገባቸውን የመምህራንና ሠራተኞች የዲስፕሊን ጉድለትና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ካልተሰጠ ህብረቱ በቀጥታ ለትምህርት ቤቱ ቦርድ /የበላይ አካል/ አቅርቦ አፋጣኝ ውሣኔ እንዲሰጥበት ማመቻቸት፤

10/ ተማሪዎች በመልካም ሥነ ምግባር እንዲታነጹ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ የሥነ ምግባር ጉድለት ያለባቸውን ተማሪዎች መምከርና መገሰፅ፣

11/ በትምህርት ቤቱ የሚዘጋጁ መመሪያዎች እና ውስጠ ደንቦችን መገምገም፣

12/ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በሚከናወኑ ተግባራት ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣

13/ አርአያነት ያለው ተግባር ላከናወኑ መምህራንና ሠራተኞች ለርዕሰ መምህሩ ለትምህርት ቤቱ ቦርድ  ማበረታቻ እንዲያገኙ አስተያየት መስጠት፣

14/ የወላጆች፣ የርዕሠ መምህራን እና የትምህርት ቤቱ ቦርድ /የበላይ አካል/ በጋራ እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

15/ ህብረቱ ከዚህ መመሪያ ጋር በማይቃረን መልኩ ስለስራው የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

16/ የትምህርት ቤቱ የበላይ አካል/ቦርድ የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት አባላት ከቦርዱ ጋር በመርህ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

17/ በት/ቤቱ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርአትን ተከትሎ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ተቀብሎ ይመረመራል የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

## 10.<u>የወላጆች ተማሪ መምህር ህብረት ሰብሳቢ ተግባርና ሃላፊነት</u>

ከላይ በተራ ቁጥር 9 ለህብረቱ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በበላይነት የሚፈጽም ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል

1/ የወላጅ፣ተማሪ መምህር ህብረት እቅድ በጋራ ያዘጋጃል፤

2/ ከትምህርት ቤቱ ቦርድ ሰብሳቢ/ ርዕሰ መምህር ጋር በመሆን የወላጆች ጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ አጀንዳዎች ይቀርፃል

3/ የትምህርት ቤቱን የወላጆች ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ከት/ቤቱ ርእሰ መምህር ጋር ይመራል፤4/ የህብረቱን ስብሰባን ይመራል፣

5/ የትምህርት ቤቱ እና የወላጆች የግንኙነት ጊዜን ያስወስናል፤

6/ጊዜን ጠብቆ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤

**11.<u>የህብረቱ ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

1/ ሰብሳቢው በማይገኝበት ወቅት እሱን ተክቶ ይሰራል፤

2/ በሰብሳቢው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል ፤

**12.<u>የወላጆች ተማሪ ህብረቱ ፀሃፊ ተግባርና ሃላፊነት</u>**

1/ የስብሰባ አጀንዳዎችን ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር አዘጋጅቶ ያቀርባል

2/ የወላጆች ጠቅላላ ጉባኤ እና የህብረቱን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፤ ያደራጃል፤ ከሚቀጥለው ስብሰባ በፊት እንዲያውቁትም ያደርጋል፤

3/ ህብረቱን እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

4/ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ያደራል፡፡

**13.<u>የህብረቱ አባላት ተግባርና ሃላፊነት</u>**

1/ የህብረቱ ውሳኔዎችን በጋራ መወሰን

2/ የግንኙነት ጊዜን ጠብቆ በስበሳቢዎች ላይ መሳተፍ

3/ የብረቱን ተግባርና ሃላፊነቶችን በጋራ ማከናወን

**14.<u>ክልከላ</u>**

1/ የህብረቱ አባላት ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸው ከሃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ የተለየ ጥቅም ማግኘት የለባቸውም፡፡

2/ ማንኛውም የህብረቱ አባል በትምህርት ቤቱ ኮሚቴ አባልነት ከተሰጡት ተግባርና ሃላፊነቶች ውጭ ማናቸውንም ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት፣ ከማንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በትምህርት ቤት ውስጥ አጀንዳ አድርጎ መወያየትና አቋም መያዝ አይቻልም፡፡

3/ የህብረቱ አባል ከተሰጠው ተግባርና ሃላፊነት ውጭ በትምህርት ቤቱ ሌሎች ስራዎች ገብቶ ተፅእኖ መፍጠር አይችልም

4/ የህብረቱ አባል ከተቀመጠለት ተግባርና ኃላፊነት ውጭ በት/ቤቱ ጋር ግላዊ/ በተናጥል ጥቅምን መሰረት ያደረገ ስምምነት ማድረግ አይችልም፡

5/ የህበረቱ አባል መምህር በአባልነት ምክንያት ከትምህርት ቤቱ የሚያገኛቸው ጥቅሞች አባል በመሆኑ ምክንያት ማቋረጥ አይቻልም፡፡

6/ የህብረቱ አባል የ ሆነ የተማሪ ወላጅ በህብረቱ እንዲያገለግል ተመረጠ በኋላ ልጁ ነጻ የትምህርት እድል ቢያገኝ ወላጁ ከህብረቱ እንዲወጣና በሌላ እንዲተካ ይደርጋል፡፡

7/ በትምህርት ቤቱ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚደገፍ ተማሪ ወይም ወላጅ የህብረቱ አባል መሆን አይችልም፣

## ክፍል ሶስት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 15.የትምህርት ቤቱ ቦርድ /የበላይ አካል/ ኃላፊነትና ተግባራት፣

የትምህርት ቤቱ ቦርድ ወይም የበላይ አካል እንደ ትምህርት ቤቶች ባህሪ እና አደረጃጀት የተለያየ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል ።

1/ ከትምህርት ቤቱ የወላጅ መምህር ተማሪ መምህር ህብረት ጋር አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሳይጨምር በየሩብ ዓመቱ ይሰበሰባል፤

2/ ሌሎች ለመማር ማስተማሩ ሥራ መጠናከር የሚያግዙ ተግባሮችን በጋራ ማከናወን።

### 16.የትምህርት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

ትምህርት ቤቱ መደበኛው የትምህርት ቤቱ ስራዎች እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ ለህብረቱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

2/ ሌሎች ለመማር ማስተማሩ ሥራ መጠናከር የሚያግዙ ተግባሮችን በጋራ ማከናወን።በት/ቤቱ የወተመህ ተሳታፊ የሆኑ መምህራን እና ተማሪዎችን ያስመርጣል፣

**17.<u>የወላጅ ጠቅላላ ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የወላጅ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት በት/ቤቱ የሚገኙ የሁሉም ተማሪ ወላጆች /አሳዳጊዎች/ ናቸው፡፡ የሚከተሉት ተግባራትና ሀላፊነቶች ይኖሩታል።

1/ በህብረቱ የ የሚሳተፉ ወላጆችን መሰየም፤

2/ የዓመቱን የህብረቱን ዕቅድ መገምገምና ማጽደቅ፤

3/ ከወከላቸው የህብረቱ አባላት መካከል ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የማይወጡትን መሻርና በአዲስ መተካት።

**18. <u>የወላጆች ተግባርና ኃላፊነት</u>**

1/ ወላጆችና አሳዳሪዎች ልጆቻቸው ወይም የሚያስተዳድሯቸው ህፃናትን ትምህርት በቅርብ የመከታተልና ትምህርታቸውን ሳያቋርጡ እየተከታተሉ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፡፡

2/ ወላጆችና አሳዳሪዎች ልጆቻቸው በሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ማክበር አለባቸው፡

3/ በት/ቤቱ ልጆቻቸውን የሚያስተምሩ ወላጆች በጠቅላላ ጉባዔ ከተመረጡ የመገልገል ሃላፊነት አለባቸው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩልዩ ድንጋጌዎች</u>

**19. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች</u>**

በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ከዚህ መመሪያ ጋር ተቃራኒ የሆኑ መመሪያዎች እና ልማዳዊ አሰራሮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**20. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>**

ትምህርት ሚኒስቴር መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማሻሻል ይችላል።

**21.<u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ እና በራሱ በፍትሕ ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ብርሃኑ ነጋ(ፕሮፌሰር)

የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር

የካቲት 29 ቀን 2016ዓ.ም